## የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ፤ ሳንፍራንሲስኮ

# የ ምር ም ር ጥ ና ት

# የተመርማሪ የግል መብት እንቀጾች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የግል መብቶች ለጥናት ተመርማሪ ሆኖ ለመሳተፍ ለሚጠየቅ ሰው ሁሉ የቀረበ ነው። የምርመራው ተከፋይ ስሆን ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መብቶች አሉኝ፥

፩) የምርመራው አላማ ምን እንደሆነ እንዲነገረኝ፤

፪) በምርመራው ከሚጠቀሙት መድሃኒቶችና የሕክምና መሳርያዎች አጠቃቀም ከመደበኛ የህክምና ዘዴዎች ምን ልዩነት እንዳላቸውና ምን ጉዳት በሰውነቴ ወይም በህይወቴ እንደሚሰማኝ እንዲነገረኝ፤

፫) ምርመራ በሚደረግብኝ ጊዜ ምን ያህል ጉዳት ወይም ጭንቀት በሰውነቴ ላይ እንደሚያደርስብኝ እነዲነገረኝ፤

፬) በምርመራው ስሳተፍ ምን አይነት ጥቅም እንደማገኝበትና ጥቅሙም ምን እንደሆነ እንዲነገረኝ፤

፭) ከዚህ ሌላ በተጨማሪ ሌሎች ምን ዓይነት ምርጫዎች እንዳሉኝ ምርጫዎችም ምርመራ ከሚደረግብኝ የተሻሉና ያልተሻሉ መሆናቸው እንዲነገረኝ፤

፮) ምርመራው ከመጀመሩ በፊትና በሚካሄድበት ግዜ ማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ስለምርመራው ለመጠየቅ መብት እንዳለኝ፤

፯ በምርመራው ላይ ድንገት በህክምና ጉድለት ቢደርስብኝ ምን አይነት የተለዩ የህክምና ምርጫዎች እንዳሉኝ እንዲነገረኝ፤

፰) ምርመራ ከተጀመረ በኋላ ሃሳቤን ለመቀየር መብት እንዳለኝ፣ በምርመራው አለመካፈሌም ለመታከምና ለመመርመር ያለኝን መብት እንደማያጓድለው፤

፱) በስምምነት የተፈራረምንበት፤ የስምምነቱም ቀን የተጠቀሰበት ወረቀት ግልባጭ እንዲሰጠኝ።

፲) በምርመራው ለመሳተፍ እንድስማማ ምንም አይነት ግፊትና ተጽዕኖ እንዳይደረግብኝ።

________<>________

ምንም ዓይነት ጥያቄ ቢኖረኝ የምርመራውን ኃላፊ ወይም አረዳት መጠየቅ እችላለሁ። በተጨማሪም የሰው የጥናት ምርመራ ድርጅትን ስለመብቴ ለማነጋገር የኮሚቴውን ቢሮ በሚቀጥለው ስልክ ቁጥር (415) 476-1814 ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 8ሰዓት እስከማታ 5ሰዓት መገናኘት እችላለሁ። ወይም ከዚሁ ድርጅት በሚቀጥለው አድራሻ በደብዳቤ ግንኙነት ለማድረግ እችላለሁ።

አድራሻ
Committee on Human Research
University of San Francisco
San Francisco, CA 94148.